በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - ክፍል 1

**መምህር፡-  ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፦</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥቅምት ፳፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# <u>የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በቤተ ክርስቲያን</u>

- ከዚህ በፊት እንደተማርነው ሰባቱንም ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለመፈጸም 3ት ነገሮች ያስፈልጋሉ፡፡ እነርሱ

1.ምሥጢራቱን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ነገሮች ለምሳሌ ውሃ ለጥምቀት.... ወዘተ

2.ምሥጢራቱን የሚፈጽሙ ካህናት /ቀሳውስትና ጳጳሳት/ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን መሠረት፡፡

3.በምሥጢራት ጸጋ የሚያድለው የመንፈስ ቅዱስ አሠራር፡፡

<u>በምሥጢረ ጥምቀት፡</u>

- መንፈስቅዱስ የምንጠመቅበትን ውሃ በጸሎቱና በቡራኬው አማካይነት ለዳግመኛ ልደት የሚያበቃ አድርጎ ይለውጠዋል፡፡ -
- ተጠማቂውንም ነፍሱን በማንጻትና አዲስ ሕይወት በመስጠት ይቀድሰዋል፡፡

***-"ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና፡፡" <u>ሮሜ. 6፤9</u>***

***-"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት አይችልም፡፡" <u>ዮሐ.3÷5</u>***

***-"አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀብላችሁ.....የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፡፡" <u>ሮሜ. 8፤15-16</u>***

***-" ያመነ የተጠመቀ ይድናል፡፡ ያላመነ ግን ይፈረድበታል፡፡ " <u>ማር. 16፡16</u>***

***-"ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፣ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፤እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም፤ያን መንፈስም በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፣በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡" <u>ቲቶ.3፤4-7</u>***

<u>በምሥጢረ ሜሮን፡</u>

- በዚህ ምሥጢር የመንፈስ ቅዱስን ተስጥዖና ጸጋ ስናገኝ፣በዚህም በእምነትና በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የሚያስችለንን ኃይል እንቀበላለን፡፡ በተጨማሪም አካላቶቻችንና ስሜቶቻችንም ይቀደሳሉ፡፡

***-"በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚየጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው፡፡" <u>2ኛ ቆሮ. 1፡21-22</u>***

***-"እናንተም ከቅዱስ ቅባት ተቀብላችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡" <u>1ኛ ዮሐ. 2፤20</u>***

# የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በቤተ ክርስቲያን

***በምሥጢረ ንስሐ፡***

- እግዚአብሔር ስንወድቅ ዳግመኛ የሚያነጻንን ምሥጢረ ንስሐን በቤተክርስቲያን ሠጠን፡፡(ይህ የሚሆነውም ንስሐ ገብተን ስንቆርብ ነው፡፡) "እውነት እላችኋለሁ፣ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡" ***ማቴ. 18፣18***
- "ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡-መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቅርላቸዋል የያዘችኊባቸውም ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡" ***ዮሐ. 20፣22-23***

***በምሥጢረ ቁርባን፡***

- ካህኑ በሥርዓተ ቅዳሴው ሲጸልይ መንፈስ ቅዱስ ለሁለት ነገር ይመጣል ፡- ኅብስትና ወይኑን የጌታ ሥጋና ደም አድርጎ ለመለወጥ እና የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል የበቃን እንድንሆን፡፡

***በምስጢረ ቀንዲል፡***

- ካህኑ ሕሙሙን በቅዱሱ ቅባት (ቀንዲል) ሲቀባው በመንፈስቅዱስ ኃይልና ሥራ በሽተኛው በሥጋና በነፍስ ይድናል፡፡ "የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል፤ ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል" ***ያዕ. 5፣14*** "ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው፡፡" ***ማር. 6፣13***

***በምሥጢረ ተክሊል፡***

- ተጋቢዎቹ እንድ የሚሆኑበት ይህ ምሥጢር በቤተክርስቲያንና በክርስቶስ ካለው አንድነት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ "ለእያንዳዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ፡፡ ሚስቶስች ሆይ ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፡፡" ***ኤፌ 5፣21-22*** " ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ይሆናሉ፡፡“ ***ማቴ 19፡5፡፡***
- ይህ የሚመላውና የሚፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ሁለቱ ሰዎች በእምነት፣በፍላጎት፣በዓላማቸውና በፍቅር አንድ ይሆናሉ፡፡

***በምሥጢረ ክህነት፡***

- በቤተክርስቲያን ሦስት የክህነት ማዕረጋት አሉ፡፡ (ዲቁና፣ ቅስና ጵጵስና) መንፈስቅዱስ በሁሉም ማዕረጋት ይሠራል እያንዳንዱ በሥራውና ለእግዚአብሔር በሚሠጠው አገልግሎትም እንዲከናወንለት ይረዳዋል፡፡
- ዲያቆናት በጥበብና በብቃት ሕዝቡን የሚያገለግሉበት ጸጋና ምክር ከመንፈስቅዱስ ያገኛሉ፡፡
- ካህናት ሕዝቡን ለማገልገል መንፈሳዊ ምሪት እና ብቃትን ከመንፈስቅዱስ ይቀበላሉ፡፡

# የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በቤተ ክርስቲያን

- ጳጳሳት አብያተክርስቲያናትን የመከታተልና የማስተዳደር ኃላፊነትን እንዲወጡ መንፈስቅዱስ ያግዛቸዋል፡፡
- መንፈስቅዱስን ቤተክርስቲያንን ለማሳደግ ይሠራል በሐዋርያት ሥራ የመንፈስ ቅደስ ኃይልና ሥልጣን የምናነብባቸው ብዙ ታሪኮች ተጽፈዋል፡፡
- መንፈስቅዱስ የሐዋርያትን ስብከት ሲመራና ቤተክስቲያንንም ሲያሳድግ እናገኛለን፡፡ ***<u>የሐ.ሥ. 8:26-40፣10፣17-33፣ 13:2-4</u>***
- የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምዕመናን ለማሳደግ፡- ሦስቱ አካላት (ሥላሴ) በእኛ ማዳን ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ አብ በፍቅር ወልድ በመስዋዕትነትና በጸጋ መንፈስ ቅዱስ በመምራትና በተሰጥዖ፡፡ በዚህ ምክንያትም ነው ካህናት በቅዳሴያቸው ሲጸልዩ "የእግዚአብሔር ፍቅር ወልድ ጸጋ መንፈስቅደስ ኅብረት ከእናንተ ጋር ይሁን" የሚሉት፡፡ ***<u>ካል ቆሮ 13፡14፡፡</u>***
- በርግጥም ይህን የሚደግፉ በርካታ የመጽሐፍቅዱስ ጥቅሶች ታገኛላችሁ፡፡ ከሦስቱ (ሥላሴ) እርዳታና አሠራር ውጪ ማንም እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንና ሰማያዊ ርስት ማግኘት አይችልም፡፡

***<u>የሚከተሉት መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ያለውን አሠራር ያሳዩናል፡፡</u>***

- ***<u>የእግዚአብሔር ልጅነት በመንፈሳዊ ልደት</u>*** (ጥምቀትና ሜሮን) እና በክርስቶስ አዳኝነት ስናምንና ስንጠመቅ በመንፈስ ቅዱስ አሰራር የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን፡፡ “በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፡፡ አባ አባት ብለን.....የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀብላችሁ......የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፡፡" ***<u>ሮሜ. 8፣15-16</u>***
- ***<u>ወደ እውነት መምራት</u>*** መንፈስቅዱስን በውስጣቸው ያሳደሩ ሰዎች ፍላጎቶቻቸውን ይቆጣጠራሉ፡፡ወደ እውነት መርቶም ያደርሳቸዋል፡፡ "እኔም አብን አለምናለሁ ፤ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፡፡ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ሰለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሀ፡፡" ***<u>ዮሐ. 14፣16-17</u>*** "አብ በሰሜ የሚልከው ግን መንፈስቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፡፡" ***<u>ዮሐ. 14፣26</u>***
- "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ፡፡" ***<u>ዮሐ.15፣26</u>***

# የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በቤተ ክርስቲያን

***ጥበብን መግለጥ፡-*** መንፈስቅዱስ ያደረበት ሰው መንፈሳዊ ጥበብ እና ሰማያዊ ነገርን መግለጥ ይሠጠዋል፡፡ "የክብር አባት… እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤" ***ኤፌ. 1፡17-49***

- የመንፈስ ንቃትና ንጽሕና መንፈስቅዱስ ያድሡናል፣ ያነጻናል እንዲሁም ጠባዮቻችን ቀስ በቀስ ይድስልናል፡፡ "ወይስ አመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙትን የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሐየርን መንግስት አይወርሱም፡፡ ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደእነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል፡፡" ***1ኛ ቆሮ.6፣9-11***

***እንድንጸልይ ያደርገናል*** መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ከድካማቸው እንዲበረቱ እና ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደሚገኛኙ ያስተምራል ለምሳሌ ስንጸልይ "መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን እናውቃለንና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይናገር መቃተት ይማልድልናል (ባለማወቅና በድካም የምናደርገውን ጸሎት ተሰሚ ያደርግልናል:: (ያርምልናልም፡፡) ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና፡፡(እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንዲጸልዩ ያደርጋቸዋል)" ***ሮሜ. 8፣26-27***

***በመከራችን ያጸናናል*** "አጽናኙ" (በግሪክ - ጰራቅሊጦስ) መንፈስ ቅዱስ በኃዘናችን የሚያጸናንና የሚያበረታንም ነው፡፡ "እኔም አብ እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፡፡" ***ዮሐ.14-16***

***ማጠቃለያ***

(1.)መንፈቅዱስ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይሠራልና የእግዚአብሔርን ጸጋዎች ሁሉ እንቀበላለን፡፡

(2.)መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እየሠራ መሆኑን መርምሩ፡፡ የሚሠራ መንፈስ ቅዱስ እንዳይለየን እንለምን፡፡

(3.)በመንፈሳዊ ሕይወት የመጀመሪያ ደረጃ ንስሐ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስም ንስሐ እንድንገባ ይረዳናል፡፡ ከዚያም እንደ ፍቅር፣ ራስን መካድ፣ ሰማያዊ አንድነት… ወዳሉት የመንፈስ ፍሬዎች ይመራናል፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥም ቅዱሳንን የረዳቸው እና ለጥልቅ መንፈሳዊ ደረጃ ያበቃቸው መንፈስቅዱስ ይረዳናል፡፡

# የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በቤተ ክርስቲያን

***መንፈሳዊው መንገድ***

- የንስሓ ሕይወት የመንፈሳዊ መንገድ መጀመሪያ ነው፡፡በዚህ የሽግግር ጊዜ ውስጥ ሰው በእግዚአብሔር ላይ በጠላትነት ከመነሣትና እርሱን ከመቃወም ይልቅ የእርሱን መንገድ መከተል ይጀምራል፡፡
- የአንድ ሰው ግብ የቅድስና ሕይወትን ለማግኘት ከሆነ መንገዱ ረዥም ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ቅድስናን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡፡ ".. ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፤ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና፡፡" ***ዕብ 12፡14፡፡*** እግዚብሔርም "…ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁሉ፡፡" ***(ዘሌ 19፡2)*** ብሎናል፡፡
- አንድ ሰው ሲያድግ፣ እግዚአብሔርን ምሳሌ አድርጎ ሲወስድና ወደ እርሱ መልክና ምሳሌ ሲጠጋ የሚለዋወጡ የቅድስና ደረጃዎች አሉ፡፡
- በእምነት ውስጥ ያለ ሰው እግዚአብሔር ከእርሱ እንደሚጠብቀው ከቅድስና ሕይወት ደረጃ ወደ ፍጹምነት ደረጃ የሚያነጣጥረው እንዲህ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህ ፍጹምነት እንዲኖረን ያዘዘን እንዲህ በማለት ነው፡፡ "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ፡፡" ***ማቴ 5፡44፡፡***
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ከተነጠቀ በኋላ ሰው ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውንም ቃል ሰምቶአል፡፡ እግዚአብሔር የበዙ ስጦታዎችን እውቀትን ስላደለው ስሙን በአሕዛብ መካከል እንዲሸከም አድርጎታል፤ ከሌሎቹ ሐዋርያት ሁሉ የበለጠ መከራ እንዲቀበልም ሆኗል፡፡
- ይህ ቅዱስ ጳውሎስ እርሱ ስለ ደረሰበት መንፈሳዊ ከፍታ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- "አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን እንደ ተፈጸምሁ አይደለም፤ ነገር ግን ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ደግሞ የተያዝሁ ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ፡፡….ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ወዳለውም እየተዘረጋሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ፡፡"ጳውሎስ ይህ ምክሩን ያጠቃለለው፡- "እንግዲህ ፍጹማን የሆንን እኛ ሁላችን ይህን እናስብ፤…" (***ፊልጵ 3፡12-15)*** በማለት ነው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ሊይዘው ወይም ሊያገኘው የሚሞክረውና "በፊቴም ወዳለው …" ብሎ የገለጸው ነገር ምንድር ነው? ይህን አስመልክቶ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡-"ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፤ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለመወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ፡፡" ***ኤፌ 3፡18 እና 19*** "….እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ…" የሚለው ቃል ምንኛ ድንቅ ነው! ፍጹምነት በመንፈሳዊው መንገድ ውስጥ ማብቂያ የለውም፡፡አንዱን ደረጃ ስታልፍ ዕድገት ያመጣህ መስሎ አይሰማህም፤ስለሆነም በጸጸት ሌላ ትጨምራለህ፡፡አድማሱን የምታሳድድ ሰው ነው የምትመስለው፤ምድርና ሰማይ የሚገናኙበት ነው ብለህ የምታሰብበት ቦታ ላይ ስትደርስ ከፊትህ ማብቂያ በሌለው ሁኔታ ተዘርግቶ ይጠብቅሃል፡፡ ጉዳዩ እንዲህ የሚቀጥል ከሆነ ወደ ፊት እንቀጥል፡፡ እስከ አሁን ንስሓ ላይ ካልደረሰን የመንገዱ መጀመሪያ እርሱ ነው፡፡

# ቤተክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት

***የቤተክርስቲያንን ታሪክ ለምን እናጠናለን?***

- ስለቤተክርስቲያን ታሪክ ስናጠና በምድር ስላለው የእግዚአብሔር መንግስት ማጥናታችን ነው፡፡ የመንግስቱ አጀማመር መስፋፋቱና የሰው ልጆች ድህነትም የታሪኩ አካላት ናቸው፡፡
- የቤተክርስቲያን ታሪክ "የሰናፍጭ ቅንጣት" ወይም "ዳቦን ሁሉ የሚያቦካ እርሾ" ተብሎ በጌታችን የተመሰለው ምሳሌ ቀጣይ ክፍልና ማብራሪያ ነው፡፡ "መንግስተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፈጭ ቅንጣት ትመስላለች እሷም ከዘር ሁሉ ታንሳለች ባደገች ጊቼ ግን ከአትክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መተው በቅርንጫፏ እስኪሰፍሩ ዛፍ ትሆናለች፡፡ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፡- መንግስተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች፡፡" ***ማቴ. 13፥31-33***
- የቤተክርስቲያን ታሪክ የእግዚአብሔር ኃይልን በዲያሎስና ኃይሎቹ ላይ ያለውን ድል እንዲሁም የብርሃን መንግስት ከጨላማው መንግስት በላይ ያለውን ጥንካሬ የምናይበት ነው፡፡
- የቤተክርስቲያን ታሪክ የተሻለው የክርስትና መገለጫ ነው፡፡ የሰው ዘር ሃይማኖታዊ እድገትና የእግዚአብሔርን የማዳን እቅድ ያሳየናል፡፡
- የቤተክርስቲያን ታሪክ የክርስቲያኖች ብርታትና ጽናት ነው፡፡ "እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወገድን የእምነታችንንም ራስና ፍጻሜውን እየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትእግስት እንሩጥ" ***ዕብ. 12፥1***

***የዘመነ ሐዋርያትን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የማጥናት ጥቅም***

- ዘመነ ሐዋርያት ዋናው የቤተክርስቲያን ምንጭ እና መሰረት ነው፡፡ ይህ ዘመንም መንፈስ ቅዱስ የሐዋርያትን ሥራ በሙሉ ይመራበት የነበረ ዘመንና ሐዋርያት ከዛ በኋላ ላለው ዘመን ሁሉ የሚሆነውን ሁሉ የሰሩበት ዘመን ነው፡፡
- ዘመነ ሐዋርያት የክርስትናን ውጤታማነትና ንጽህና የሚያሳይ የእምነት ሥዕል ነው፡፡
- ይህም የክርስትና ሃይማኖት ከሰው ልጆች ሥራ ሁሉ የእግዚአብሔር ሥራ የሚበልጥ መሆኑን የሚያረጋግጥልን ነው፡፡ መልካም ምሳሌ የሚሆኑን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅዱስ ማርቆስና ቅዱስ ዮሐንስ ዓይነት አርአያዎቻችንን የሚያሳየን ዘመን ነው፡፡

# ቤተክርስቲያን በዘመነ ሐዋርያት

***<u>የዘመነ ሐዋርያት ታሪካዊ ምንጮቻችን</u>***

- የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተለይም የሐዋርያት ሥራ ፡፡
- የሐዋርያት የትምህርትና የሕግ መጻሕፍት ለምሳሌ፡- መጽሐፈ ዲድስቅልያ
- የሐዋርያውያን አበው (የሐዋርያት ተከታይ የነበሩ ናቸው፡፡) ጽሑፎች፡- ለምሳሌ የሮማው ቀሌሜንጦስ፣ አግናጢዮስና ፖሊካርፐርስ… የመሳሰሉት
- አይሁዳዊ ምንጮች ለምሳሌ፡- የፊሎና ዮሲፉስ ጽሑፎች
- በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበው መጻሕፍት፡፡ ማለትም ሁለተኛው የሐዋርያት ትውልድ የዚህ ምንጭ ምሳሌዎቻችንን ዮስጢኖስ ፣ ኢራያዎስ እና ሄጂሲፐስ ናቸው፡፡

***<u>ዘመነ ሐዋርያት ማለትን ምን ማለት ነው?</u>***

- ይህ ዘመን ከ34 ዓ.ም እስከ 100 ዓ.ም ያው ዘመን ነው፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት የጰንጠቆጤ ዕለት ዮሐንስ እስከ ተሠወረበት ዓመት ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከሐዋርያት ረጅም እድሜ የኖረ ሐዋርያ ነው፡፡

***<u>ቤተክርስቲያን በተወለደችበት ዘመን የነበረው ዓለም</u>***

- ይህን ጉዳይ ለመመልከት ሦስት ክፍሎን ማንነት ይጠበቅ ብንል:-

1. **አይሁድ**: በውስጣቸው የነበሩ ክፍሎችን ልማዳቸው ወ.ዘ.ተ
2. **አሕዛብ**: ጣዖት ያመልክ የነበረው ዓለም
3. **በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ፡፡**

***<u>ይህ ትምህርት</u>***

- ውድ የሆነችውን የቤተክርስቲያናችን ታሪክ ማጥናት እንድኖርባትና እንድንከተላት ይረዳናል፡፡ እንደሁም አዳዲስ የሐሰት ትምህርቶችንና ከእውነተኛይቱ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ያፈነገጡ ሐሰተኞች የሆኑ አዳዲስ የዓለም “ሃይማኖቶችን” እንድንቋቋም ያስችለናል፡፡
- ቤተክርስቲያናችን ታካዊት ናት፡፡ ብዙ በጣም ብዙ ዓመታት ወደ ኋላ የሚመልሰን መሠረት አለን፡፡ ጠንክረን እንድንቀጥል ከሥራችን ጋር መገናኘት አለብን፡፡
- በዚህች ድንቅና ውድ ቤተክርስቲያን እንኮራለን ማለት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ዋናው መስመር በእውነት በፍቅር ውስጥ ነን? ይህንስ በድርጊቶቻችን ለሌላው እንገልጻለን ? ለሚለው ተገቢ መልስ ይዞ መገኘት ነው፡፡

# … ይቀጥላል

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf:

www.zeorthodox.org